EthioLion

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

የካቲት 19/2002 ዓ.ም.

# ጥሪ ለኢትዮጵያዊያን ሴቶች እናቶቻችንና እህቶቻችን

ማህበራዊ መረጋጋት፣ ሰላምና ፍትህ የሰፈነባት፤ የፆታ እኩልነት፣ የሕግ የበላይነት፣ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበርባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል ስኬታማ ይሆን ዘንድ የሕብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑት ሴቶች ሙሉ ተሳትፎ ማድረግ በጣም ወሳኝ መሆኑን በተደጋጋሚ ይፋ ያደረግነው ከዋነኛዎቹና ፅኑ የሆነ አቋማችን ነው። ሴቶችን የነጻነት አየር እንዲተነፍሱ በማድረግ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ መድረኩን የማያመቻችላቸው ሕብረተሰብ በዴሞክራሲ ሥርዓት ይተዳደራል ለማለት የሚከብደን ከመሆኑ ሌላ ምን ተይዞ ጉዞ ነው ብንል ሀቁን መናገር ነው የሚሆነው።

ሀገራችን በአሁኑ ወቅት የምትገኝበት ሁናቴ ከእናቶቻችንና ከእህቶቻችን እንዲሁም ከድርጅቶቻቸው ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዲደረግ ጥሪ ማቅረብን የሚጠይቅ ለመሆኑ ግልፅ ነው። ኢትዮጵያ ሀገራችን የድረሱልኝ ኡኡታዋን ሰምቶ መልሱን ለመስጠት ከምንጊዜውን በበለጠ ሕሊናን ክፍት አድርጎ ጆሮ መስጠት ወቅቱ አሁን ነው ብንል ከአገዛዙ ደጋፊዎች በስተቀር የሚቃወመን ሊኖር አይችልም። እናንት እናቶቻችንና እህቶቻችን ያንን ሰው በላ የሆነ የደርግ አረመኔ አገዛዝን ለማስወገድ ከወንድሞቻችሁ ያላነሰ በከተማው በገጠሩ፣ በጫካውና በዱር በገደሉ፣ ደማችሁን አፍስሳችሁ አጥንታችሁን ከስክሳችሁ የትግል ታሪክ ብታስመዘግቡም የነጻነት መብት ተጎናፅፋችሁ የመብቶቻችሁ ሙሉ ተጠቃሚ ለመሆን አልተቻላችሁም። እየደረሰባችሁ ያሉት ጭቆናና በደል መልካቸውን በመቀያየር እየተለዋወጡ በይዘት ግን ካለፈው ሥርዓት ጋር አንድ ሆነውና ከሀገር ሕልውና ጥያቄ ጋር ተዛምደው በባሰ ሁናቴ ቀጠሉ እንጂ አልተወገዱላችሁም። ለዚህ ለአሁኑ ሁናቴ በዋናነት ተጠያቂው ላለፉት 18 ዓመት በሥልጣን ላይ የተቆናጠጠው የመለስ አገዛዝ የሚከተለው ጎጠኛ ፖሊሲው መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ አገዛዝ ደግሞ ሕዝብን ለመጨቆን ከሚጠቀምበት የጸጥታ፣ የፖሊስና የጦር ተቋማቱ ላይ ከመንጠልጠል በስተቀር ምንም ሕዝባዊ ድጋፍ የሌለው፤ በአልሞት ባይ ተጋዳይ እየተንፈራገጠ እዚህም እዚያም በሴቶች እናቶቻችንና እህቶቻችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ያለ ነው። ነገ ተነገወዲያ ሳይሆን ትላንት ከትላንት ወዲያ መወገድ የነበረበት ጎጠኛ አጥፊ ቡድን መሆኑን የምታውቁት ነው፤ የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ለናንተ የተሰወረ አይደለም።

ሕጋዊ መብቶቻችሁ አልተከበሩላችሁም። በወሬ እንጂ በተግባር እኩልነታችሁ አልተረጋገጠላችሁም። የረሃብ፣ የችጋርና የድርቅ ሰለባ መሆናችሁ - በተለይም በገጠሩ ላላችሁት - አላቆመላችሁም። በትምህርት መታነጽ በሚገባችሁ በልጅነትና በወጣትነት እድሜያችሁ በጠለፋና በሌሎችም ምክንያቶች የምትፈናቀሉትና ለመንገድ አዳሪነት፤ ለአልባሌ ተግባራቶች የተጋለጣችሁ መሆናችሁ እንደቀጠለ ነው። በየቤቱ እያንኳኳ በሚገባው ቀሳፊ የኤድስ በሽታ በብዛት እየተጠቃችሁ ያላችሁት እናንተ ለመሆናችሁ በእለት ተዕለት ኑሯችሁ የምታዩትና

EthioLion.Com

የምታውቁት ነው። በሥነ ተዋልዶ ጤና ችግርና ኤድስ እናንተ ብቻ ሳትሆኑ የምትወልዷቸው ሕጻናትም ለአቅመ ሄዋን ደርሰው ጤናማ ኑሮ ለመኖር ያላቸው እድል በእንጭጭነታቸው ሲቀጭ የሀዘን፣ የጭንቀት ጫናው እንዴት እንደሚያጉላላችሁ ከናንተ በላይ የሚገነዘብ ሊኖር አይችልም።

ለአቅመ ሄዋን ሳትደርሱ የምትዳሩት፤ ከጠዋት እስከ ማታ አድካሚ በሆነ ሥራ ተጠምዳችሁ ምንም አይነት የአካልና የመንፈስ እረፍት እያጣችሁ የምትገፉት የኑሮ ሁናቴ አሳዛኝና አሳፋሪነቱን በሚገባ የምታውቁት ነው። በዚህ ላይ የምትሸከሙት የቤተሰብ ኃላፊነት ከወንዱ የሚበልጥ እንጂ ያነሰ ባይሆንም በወንድ ትምክህት የሚደርስባችሁ የዝቅተኝነት ስሜት ከናንተ አልፎ ወደ ሴት ልጆቻችሁ እንዲተላለፍ በሚያደርግ ባሕል ትሰቃያላችሁ። አደባባይ የማይወጣ በቤተሰብ ብቻ የሚታይ የድብደባና ጭካኔ ለተሞላበት በደል ፍትህ የማግኘታችሁ ሁኔታ የጠበበ ነው። በገዛ ሀገራችሁ በተወለዳችሁበትና ባደጋችሁበት አካባቢ ከሚደርስባችሁ በደልና የመብት ረገጣ ለመላቀቅ በብዙ ሺህ የምትቆጠሩት ወጣት ልጃገረዶች ለቤት ሰራተኝነትና ለሌላም ወደ አረብ ሀገር መሰደድ ተዳርጋችሁ የምትኖሩበትን ሁናቴ ማውሳቱ ራሱ የሚዘገንን ነው።

ታዲያ እነዚህ ሁሉ በደሎችና ጥቃቶች በተስፋፉበት ሀገራችን የሴቶችን ጉዳይ ልዩ ትኩረት ሳይሰጥ የሚፈጸምባቸውን አድልዎና የመብት ረገጣ ማስቆም ሳይሆን እየተባባሰ በሚሄድበት ሁኔታ፤ የሴቶችን ተሳትፎ ከወንዱ ጋር በማናቸውም መድረክ በእኩል ከመስተናገዱ በፊት ድህነትን እናጠፋለን፤ ሴቶች በብዛት ተጠቃሚ የሚሆኑበት የኤኮኖሚ እድገት እናመጣለን የሚለው የመለስ አገዛዝ ፕሮፓጋንዳ ውሃ የማይቋጥር መሆኑ ከናንተ በላይ የሚያውቅ የለም። የአገዛዙ አባላትና ደጋፊ የሆኑ ሴቶች ስላለፈላቸው ብቻ እናንተንም ተጠቃሚ እያደረገ የሚነዛው ፕሮፓጋንዳ ዕውነት-የለሽነቱና አስለቺነቱም ለናንተ ባይተዋር አይደለም። በተለያየ ደረጃ ለመለስ አገዛዝ ተቃውሞ በማሰማታችሁ ሴት እናቶችና እህቶች፣ ለእስርና ለስደት የተጋለጣችሁ፤ ደብዛችሁ እንዲጠፋ የተዳረጋችሁ በርካታዎች ናችሁ። ለዚህ ሁሉ ጭንቀታችሁ ተጠያቂ የሆነው የመለስ አገዛዝ ግን ባለፈው ምርጫ ቢሸነፍም የስንቶቻችሁን ደም አፍሶ፤ ሕይወታችሁን አጥፍቶ፤ አካለ ሰንኩል አድርጎ በጉልበትና በባዕዳን በመታገዝ ሥልጣኑን ጨምድዶ ይዞ፤ ይህ መሰሪ የሆነ ጥፋቱ ተረስቶለት በምርጫ ተውኔቱ ተሳታፊ እንድትሆኑና ሕጋዊ ይሁንታችሁን እንድትለግሱት እያዋከባችሁ እንዳለ የምታዩትና የምትገነዘቡት ነው። ይህ ሰብዓዊነት የጎደለው እኩይ ድርጊት በምንም ዓይነት ተቀባይነትና ተደማጭነት ሊያገኝ የማይገባው ተግባር በመሆኑ ከሚያቀነቅነው ሥርዓት ጋር በሕዝባዊ ትግል መወገድ ያለበት እንደሆነ ሀገር ወዳድና ለሕዝባቸው ቀናዒ የሆኑ እናቶችና እህቶች የሚስማሙበት ነው።

በመሆኑም በወያኔ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻችሁ ያልተከበሩበት፤ የፆታ እኩልነታችሁ ያልተረጋገጠበት፤ የታሰሩ ወንድም፣ እህትና ልጆቻችሁ ሳይፈቱ፣ ደብዛቸው የጠፋበት፤ የቅርብ ዘመዶቻችሁና



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

Ethiopia will prevail !

ጓደኞቻችሁ የት እንደደረሱ ግልጽ ያልተደረገበት፤ የናንተንም ሆነ የሀገራችሁን የወደፊት እጣ ፈንታም ልትወስኑ እማትችሉበት ሁናቴ ነው ያለው። እነዚህ ሁሉ እንዳሉ ሆነው፣ እሱ አሸናፊ የመሆኑ ጉዳይ አስቀድሞውኑ ዝግጅቱን ባጠናቀቀበት፤ የምርጫ ካርድ ከሳጥን ውስጥ እንድትከቱለት ብቻ እያደረገባችሁ ያለውን ተጽዕኖ ተቋቁማችሁ፤ የተአቅቦ መፈክር አንግበው ወያኔን ወግድልን ከሚሉት የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጎን እንድትቆሙና ይህንን ኃይል እንድታጠናክሩ ኢሕአፓ የትግል ጥሪውን ያቀርብላችኋል። የወያኔ ምርጫ ነጻና ፍትሃዊ ሊሆን የሚችልበት ምንም የለምና የናንተም፣ ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብም ምርጫ አይደለም። ስለዚህም በመጪው ምርጫ ተብዬ ሂደት አለመሳተፍ ብቻ ሳይሆን የምርጫውን ሂደት ራሱንም መቃወም የዜግነት መብታችሁ መሆኑን ተገንዝባችሁ ታገሉት። በወያኔ ምርጫ ለመሳተፍ የተሰለፉትን ደግሞ ጠላትን ማፍቀር ከመጀመር በፊት ወዳጅን በጥሩ መንከባከብ የሚመረጥ መሆኑን በማስታወስ በምርጫው ተካፋይ አትሁኑ የሚል ጥሪ እያስተላለፋችሁ፤ ሊታረሙ የሚችሉትን እንዲታረሙና ከሕዝቡ ጎን እንዲቆሙ በሴትነት እይታችሁ ምክራችሁን ለግሷቸው። አሻፈረን የሚሉትን ደግሞ ሕዝብን መካድ መሆኑን በማሳወቅ ከሕዝብ እንዲነጠሉ በሕብረት ታገሏቸው። የወቅቱ ግዴታ በምርጫ መሳተፍ ሳይሆን ሀገርን ማዳን መሆኑን ማስገንዘብ ደግሞ ሀገራዊ ግዴታ ነውና። የታሰሩ ዜጎች እንዲፈቱ፤ ለም መሬታችንን መቸብቸቡና ምርቶቿን ወደ ባዕድ ሀገር ማጓጓዙ እንዲቆም፤ ለሱዳን የተሰጠው መሬት እንዲመለስና የሱዳን ጦር ከኢትዮጵያ ምድር እንዲወጣ፤ በአባይ ውሃ የተነሳ ብሔራዊ ጥቅማችንን የሚጻረር ድርጊት በአስቸኳይ እንዲቆም፤...ወዘተ በሚሉና በመሳሰሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ትግሉን ማፋፋም ወቅታዊ ግዳጅ ሆኖ ከፊታችን ተደቅኗል። ለዚህም የተደራጃችሁት ይበልጥ እንድትጠናከሩ፤ ያልተደራጃችሁ ደግሞ ተደራጅታችሁ በሀገርም በውጭም ተደራጅተው ከሚገኙት ጋር እያቀነባበራችሁ የምርጫ ተአቅቦ መሪ መፈክር ሥር ትግሉን እንድታፋፍሙ፤ እንዲሁም ሀገር አድን ትግሉን የላብ አደሩ፣ የሠርቶ አደሩና የአርሶ አደሩ መሰረታዊ መብቶች ሁሉ የሚከበሩበት፤ የሀገር አንድነትና ሉዓላዊነት የሚረጋገጥበት ሥርዓትን እውን ለማድረግ የሚካሄደውን ትግል እንድታቀጣጥሉ ኢሕአፓ ዳግም ጥሪውን ያስተላልፍላችኋል።

ትግላችሁ በወንድ ሞግዚትነት እንደማይካሄድ ከናንተ በላይ የሚያውቅ ሊኖር አይችልም። ሴቶች እህቶችና እናቶችን የማደራጀቱና የማታገሉ ተግባር በነቃችሁትና በተደራጃችሁት ሴቶች ትከሻ ላይ ቢወድቅም ኢሕአፓ እንደድርጅት ነጻ የሆነ፤ እናንተው ሴቶች ራሳችሁ የምትመሩትና የምትቆጣጠሩት ድርጅታችሁን ሊንከባከብላችሁ፤ ትግላችሁንም ለመደገፍ ምንጊዜም ዝግጁነቱን ሲገልጽላችሁ ለጋራ ትግላችን መሳካት የናንተ ድርጅት መኖሩ ወሳኝ ስለመሆኑ የጠበቀ እምነቱንም እያበሰረላችሁ ነው።

ያለ ሴቶች ተሳትፍ ትግላችን አይሰምርም!!
ነጻ የሴቶች ድርጅት ይለምልም!!



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

EthioLion.Com